IB DIPLOMA PROGRAMME
PROGRAMME DU DIPLÔME DU BI
PROGRAMA DEL DIPLOMA DEL BI



**AMHARIC A1 – HIGHER LEVEL – PAPER 1**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU SUPÉRIEUR – ÉPREUVE 1**
**AMHARE A1 – NIVEL SUPERIOR – PRUEBA 1**

Monday 10 May 2004 (afternoon)
Lundi 10 mai 2004 (après-midi)
Lunes 10 de mayo de 2004 (tarde)

2 hours / 2 heures / 2 horas

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a commentary on one passage only.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N’ouvrez pas cette épreuve avant d’y être autorisé(e).
- Rédigez un commentaire sur un seul des passages.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario sobre un solo fragmento.

ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ አስተያየትህን ስጥ(ስጭ)::

**1. (ሀ)**

## *ተለያየን*

"ልጄን" ብለህ ልትጠይቀኝ
በአይነ ስጋ ልትቃኘኝ
ወንዝ አቋርጠህ
አገር አልፈህ
"እንዴት ነህ ልጄ?" ብትለኝ
"አለና!" አልሁህ....
"አለን - አለን
መጥፎ አይደለም፣ ጥሩ አይደለም
ሆኖም አለን፣ አለን ይኸው
ሕይወት ጥሩ ነው፣ መጥፎም ነው
ኮምሲ - ኮምሳ ነው!" አልሁህ
ሳስረዳህ።
የልጅ ትክሻ ማቀፍን
የዘመናት ናፍቆትህን
የ'አግኝቼ ስሜው' ጉጉትህን
እያነበብሁት ራብህን
እያየሁት አይነ - ውሃህን
እጄን ሰጠሁህ እንደጊዜው
"እህስ... አገር እንዴት ነው?"
አልሁህ...
አርቄ እየጨበጥሁህ፣
እንደአገርህ መጣህብኝ
እንደአገሩ ተቀበልሁህ፣
እንደአባት በአይንህ መዘንኸኝ
እንደጊዜው ዘንበል አልሁኝ።
እና...
ገና እንደተያየን
ተለያየን።
እኔም አባቴን ለየሁህ፣
አንተም ልጅህን ለየኸኝ።
"አለየኸኝም ልጄ?... አባትህ'ኮ ነኝ!"
ብትለኝ...
"ኖኖ ለይቸሀለሁ፣ አዎን አባት ነህ"
አልሁህ...
እንደተያየን አወቅሁህ፣
እንዳወቅሁህ ለየሁህ፣
እንደለየሁህ አወቅኸኝ፣
እንዳወቅኸኝ ለየኸኝ።
እና...
"ሻይ ቡና እንበላ" አልሁህና
ወደወሰድሁህ ተወሰድህ፣
ወስጄ "ምን ትወሰዳለህ?" አልሁህ፣
አንተም "ሻሂ" አልህ፣ "ማኪያቶ" አልሁኝ፣
"እህስ?..." አልሁህ፣ ዝም አልኸኝ፣
በአንደበትህ ዝምታና በአይንህ ትዝብት
መዘንኸኝ፣

“እህስ?...” አልሁህ፣ ዝም አልኸኝ፣
ሲጃራዬን እያቦነንሁ፤
እኔም ዝም አልሁ።
በአንዲት ጠረጴዛ ላይ
ተቀምጠን እየተያየን፣
እሚያስተሳስር ቃል አጥተን፣
አንዳች የጋራ ርዕስ ጠፍቶን፣
አባትና ልጅ ተለያይተን፣
ዝም አልን እየተያየን።

ጌትነት እንየው፡ <u>እውቀትን ፍለጋ</u>፡ **1994::**

**1. ለ**

# የተማሪ ቤት ትዝታ

ከመስፍን ሀብተ ማርያም

ያለፈ ነገር ሲያስታውሱት በጣም ያስገርማል ። እነዚያ ጓደኞቼ ሁሉ ዛሬ አጠገቤ የሉም ። ሆኖም ዐልፎ ዐልፎ ሳስታውሳቸው ሥራቸው ሁሉ ከፊቴ ይደቀናል ። የነ ምትኬ ቀልድ ትዝ ሲለኝ እሥቃለሁ ። የአጥናፉና የታምራት የኳስ ጥበብ ሲታወሰኝ ፣ እነሱን እሚያህል ተጫዋች ከቶ ያለ አይመስለኝም ። የሠፈራችንን ቡድን ካገነኑት ውስጥ የሺጥላም ይገኝበታል ። ሰባት ቊጥር ካልሆንኩ እያለ የትም ቦታ እሚጫወተው የሺጥላ፡ ኳሷን ከነሰውዬው እግር መምታት ልማዱ ነበር ። ከጒቶ በቀር እሚበግረው ስለ ሌለ ፣ እሱ ተርሲኒ ሆኖ ጎል ለማግባት የሚመጡ ሁሉ ፣ በማይደክም ሰውነቱ ፣ ጸጉሩን አሹሎ እንደ ተዋጊ በሬ ገና መንደርደሩን ሲጀምር ፣ ከቻሉ ኳሷን ነካ አድርገው ፣ አለበለዚያም ወደ ኋላቸው ይመለሱ ነበር ።

የሠፈሬ ልጆች እነዚህ ብቻ አልነበሩም ። እነ እሥራት ቂሉ ፣ እነ ወንዳፍራሽ ተንኮሉ ሁሉ አብረውኝ ይማሩ ነበር ። እሥራት ዛሬ መሐንዲስ ነው ። ወንዳፍራሽ ደሞ የስድስት ልጆች አባት ሆኗል አሉ ። ዱሮ በኛ ተማሪ ቤት በመገረፍ ደረጃ ወንዳፍራሽን እሚያህለው አልነበረም ። ትንሽም የምትወዳደረው ብርቄ ነበረች ። ብርቄ የስዋስው ጥያቄ በመጣ ቊጥር ሳትገረፍ ቀርታ አታውቅም ። ማልቀስ የምትጀምረው ግን ፣ ገና አቶ አስናቀ ያን መነጽራቸውን ሰክተው ፣ "ስም ማለት ምን ማለት ነው ?" ለማለት ሲሰናዱ ነው ። በተለይም አንድ ቀን አምስተኛ ክፍል ሳለን ዲሬክተራችንን "እሳቸው" ለማለት ፈልጋ "ዜይ" ብላ ገና ስትጀምር የሣቅነው መሣቅና ፣ በአቶ ሙላቱ የተገረፈችው መገረፍ ትዝ ይለኛል ።

በእንግሊዝኛ የቃል ጽሕፈት ጊዜ ፣ ብርቄና ወንዳፍራሽ ዐሥር ዐሥር ሳይገረፉ ውለው አያውቁም ነበር ። በነርሱ ላይ ይበረታል ለማለት ነው እንጂ 'ፒርየዱ' እንደ መለዋወጡ ሁላችንም ከቅጣቱ በያይነቱ መቅመሳችን አይቀርም ነበር ። ገና አስተማሪው በሩን ከፍተው "ጉድ ሞርኒንግ" ሲሉ የተንጠለጠልንበት ዴስክ እሥር ቤት እስኪመስለን ድረስ መርበድበድ እንጀምራለን ። ማሥመሪያው ፣ መጥረጊያው ፣ ወንበር ተሸክሞ መቆሙ ፣ እጅ ወደ ላይ አድርጎ መንበርከኩ ሁሉ ትዝ የሚለን ያኔ ነው ። ከዚያ ጥያቄው ሲጐርፍ … ያጠናው እንደ ጥይት እሩምታ ሲያንታታው … ያላጠናው ሲቀባጥር … ዱላውና ውካታው ይህ ነው አይባልም ነበር ።

አስተማሪው ወጣ ሲሉ ደግሞ ፡ ክፍላችን ሌላ መልክ ይይዛል ። እነ ሲሳይ ወደ ሠሌዳው ይሄዱና የአፍሪካን ካርታ እያጠመሙ ይሥላሉ ። ወንዳፍራሽና ምትኬ ደግሞ ቶሎ ያጠፉባቸውና የራሳቸውን ተውኔት እየሠሩ ይንጎራደዳሉ።የዘመናችን ኮሚክ ተካበ "ጉቶ" ደሞ እንደ ዶሮ እያስካካ ፡ ቀሰም እምታህል አንገቱን ሳብ መዘዝ እያረገ ፡ እጁን ክንፍ አስመስሎ እያራገበ መምህሩ ጠረጴዛ ላይ ይዘልና ይወጣል ። አንዴ ሁላችንም ስንሥቅ ወንዳፍራሽ ትእይንቱን መቀማቱ ያናድደውና ፡ "ጠረጴዛው ይሰበራል" ብሎ በጉልበት ያስወርደዋል ። ተካበ ትእይንቱን ሲያቋርጥ እነ ይልማ ትንሽ የላስቲክ ኳስ አውጥተው እዛው ቡድን ለይተው መቀባበል ይጀምራሉ ። ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ማ እንደ ወረወራት ሳይታወቅ ኳሏ በበሩ ትወጣለች ።

መስፍን ሀብተ ማርያም: <u>አባደፋር</u>: ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት: 1977::